ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)

መጋቢት 24፣ 2004ዓም

# “ሰብዓዊነትም” ጀግንነት ይጠይቃል!

## ❖ “ምንም ይዛችሁ ስላልመጣችሁ ምንም ይዛችሁ አትሄዱም”

ከደቡብ የኢትዮጵያ ክፍል ቤንች ማጂ ዞን ከተለያዩ ወረዳዎች በክልሉ አመራሮች ትዕዛዝ እንዲፈናቀሉ በተወሰነባቸው 78ሺህ በሚጠጉ የአማራ ተወላጆችና ካለፈው ሳምንት ጀምሮ ለዓመታት ከኖሩበት ቀዬ በኃይል እንዲወጡ ተደርገው መግቢያ በማጣት እየተንገላቱ በሚገኙት ወገኖች ላይ እየደረሰ የሚገኘውን ግፍ፣ መከራ፣ ስቃይና እንግልት ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) አጥብቆ ይቃወማል፤ ድርጊቱንም ያወግዛል፡፡ የአቶ መለስ አገዛዝ፣ ‹‹ለፍትህ ቆመናል›› የሚሉት ፍርድቤቶችና የደቡብ ክልል አመራሮች ይህንን ሰብዓዊ መብትን የሚጋፋና ዓለምአቀፍ ሕግጋትን የሚጻረር ተግባር ለማስቆም ባለመቻላቸውና ባለመፈለጋቸው አንድም ኢትዮጵያን **ለማስተዳደር ፈጽሞ ብቃት ስለሌላቸው ከአመራር መወገድ ያለባቸው መሆኑን ያስመሰከሩበት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለዚህና ከዚህ በፊት ለፈጸሟቸው ወንጀሎች ለፍርድ የማቅረቢያው ጊዜ ከምንግዜውም በላይ አሁን መሆኑን ያረጋገጡበትም ነው፡፡**

ይህ በዘር ማጽዳት ላይ ያተኮረ የማፈናቀል ተግባር በአካባቢው ላለፉት 30 ዓመታት ከሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በዘመነ ደርግ አሁን ደግሞ በህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ከሚኖሩበት ስፍራ ተፈናቅለው ወደ ደቡብ እንዲሰፍሩ ከተደረጉ በኋላ እዚያው የተወለዱና ከአካባቢው ሕዝብ ጋር እርስበርስ እየተጋቡ የሚኖሩ ሲሆኑ አሁን ግን በስም ‹‹አማራ›› የሚል ታርጋ ተለጥፎባቸው ለዚህ እኩይ ተግባር ተጋልጠዋል፡፡ ለመሆኑ አንድ ሰው ‹‹አማራ›› ተብሎ ለመጠራት በደም ቧንቧው ውስጥ የሚተላለፈው የደም መጠን ምን ያህል መሆን አለበት? **ህወሃት/ኢህአዴግ እስካሁን ከፈጸመው በመነሳት ይህ ተግባር አገዛዙ በቦታው ሊያካሂድ ላሰበው የኢትዮጵያን ሃብት የመዝረፍ ተግባር እነዚህ በልመና ከመሠማራት ይልቅ ጠንክሮ በመሥራት የሚያምኑና በኖሩበት አካባቢ በትጉህነታቸው የተመሰከረላቸው ሠራተኛ ኢትዮጵያውያን ዕንቅፋት ሆነው ስላገኛቸው አስቀድሞ ለማስወገድ የወሰደው እርምጃ እንደሆነ የጋራ ንቅናቄያችን ያምናል፡፡**

እንዲህ ያለውን አስገድዶ ማፈናቀልና ከመኖሪያ ቦታ የማስነሳት ተግባር በዓለምአቀፍ ሕግጋት የተወገዘ ተግባር መሆኑንና ‹‹**የሮም ሕገደንብ**›› (Rome Statute) ተብሎ በተለይ በሚታወቀው ዓለምአቀፉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (መ) ላይ የተደነገገ ነው፡፡ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (መ) ደግሞ ‹‹**ከመኖሪያ ቦታ ማፈናቀል ወይም ሕዝብን በግዳጅ ከመኖሪያ ማዛወር**›› የሚለውን ሲተነትን ‹‹**ኃይልን በመጠቀም፣ በማስገደድ ወይም አስገዳጅ ድርጊቶችን በመጠቀም ሰዎችን ሕጋዊ ሆነው ከሚኖሩበት ቦታ ዓለምአቀፍ ሕግ ከሚፈቅደው ውጪ ማስነሳት፣ ማባረር . . .**›› ማለት ነው ይላል፡፡ ህወሃት/ኢህአዴግ ‹‹**ኢትዮጵያ የዓለምአቀፍ ህግጋትን ትቀበላለች**›› በማለት በውጪው ኅብረተሰብ ዘንድ በሕግ የበላይነት የሚያምን መስሎ ለመታየት ሙከራ ቢያደርግም ‹‹**የዓለምአቀፍ ህግጋትን መቀበል**›› ብቻ **ከጥፋተኝነት አለማዳኑን እንዲያውም እያወቀ ጥፋት በሚፈጽም ላይ ቅጣቱ እንደሚከብድበት ከአቶ መለስ ጀምሮ በተዋረድ እስከ ክልል የሚገኙት ባለሥልጣናት የሚዘነጉት አይደለም፡፡**

**የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ አሁን በአማራ ተወላጆች ላይ ከሚያካሂደው ከመኖሪያ የማፈናቀል ድርጊት በተጨማሪ ‹‹አረንጓዴ›› በታየበት፣ በደን በተሞላ፣ የአገር እንጡራ ኃብት በተገኘባቸው እንደ**

ጋምቤላ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋርና ኦጋዴን ክልሎች እንዲሁም በኦሞ ሸለቆ የሚኖሩ ከ1.6 ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያንን ማፈናቀሉን፣ መኖሪያ ማሳጣቱን፣ በግዳጅ ማስፈሩን ወዘተ ተያይዞታል፡፡ ደን እየመነጠሩ አካባቢውን ወደ በረሃማነት መለወጥ ዓላማው ‹‹በረሃማነትን ማስፋፋት›› ይሁን ‹‹ልማትን ማስፋፋት›› ሰሚው ብቻ ሳይሆን ራሳቸው አድራጊዎቹ እንኳን የማይመልሱት ጥያቄ ነው፡፡ ሌላው ቢቀር የህወሃት መሪዎች የመጡበትን ክልል በውል ለሚያውቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድርጊቱ በሕግ ከማስጠየቅ አልፎ በኢትዮጵያዊ ትዝብት ውስጥ የሚጥል መሆኑን የህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ አመራሮችና ደጋፊዎች ፈጽሞ ዘንግተውታል፡፡

ይህ እንደ አፓርታይድ ዓይነት ስልትን የተከተለና በዘር ላይ የተመሠረተው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ከዚህ በፊት ኤርትራውያንን ወልደው ከብደው ከኖሩበት የኢትዮጵያ ምድር ባስወጣበት ወቅት ከአቶ መለስ ‹‹ከፈለግን የዓይናችሁ ቀለም አላማረንም በማለት ልናባርር እንችላለን›› በማለት የተሰጠው መልስ የአገዛዙን የማንአለብኝ አካሄድ በግልጽ ያሳየ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ “ኦሮሞ ስለሆንክ”፣ “አማራ ስለሆንክ” ወዘተ ወይም በሌላ አነጋገር “ትግሬ ስላልሆንክ” አባርርሃለሁ፤ ከፈለኩበት አካባቢ አስወግድሃለሁ፤ አጠፋሃለሁ የሚል የዕብሪት አካሄድ እየተከተለ ይገኛል፡፡

በሺዎች ዓመታት የሚቆጠረውን የአገራችንን ታሪክ ፍጹምና ምንም ነቁጥ የሌለበት ነበር ብሎ የሚከራከር እንደሌለ እሙን ነው፡፡ ግጭቶና አለመግባባቶች በታሪካችን ተከስተዋል፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶቹ ግጭቶች በዕርቅና በፍቅር የተጠናቀቁ ቢሆኑም ህወሃት/ኢህአዴግ ግን ለመሰሪ ተግባሩ አሁንም እንዳልሻረ ቁስል እያስነሳ ህዝብን ለመከፋፈል፣ ለማበጣበጥና ለማጨካከን እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡ ለዚህም ነው በአሁኑ ጊዜ በደቡብ ኢትዮጵያ ለዘመናት የኖሩትን የአማራ ተወላጆች የጥቃቱ ዒላማ ያደረገው፡፡ ከዚህ በፊት በተደረገ የሕዝብ ቆጠራ 2ሚሊዮን የሚሆኑ የአማራ ተወላጆች ከቁጥር እንዳልገቡ ተዘግቧል፡፡ ለመሆኑ ይህንን ያህል የሕዝብ ቁጥር የት ደረሰ? ሰዎቹስ ምን ሆኑ? ሞቱ? ጠፉ? ተነኑ? ይህ የውክልና ሥልጣናቸውን ለመሸርሸር ህወሃት/ኢህአዴግ ሆን ብሎ ያደረገው ሲሆን በግልጽ እንደታየውም ለም የሆነውን የወልቃይት አካባቢ ከአማራ ክልል በመውሰድ ለትግራይ መስጠቱ አንዱ እንደ ማስረጃ የሚጠቀስ ነው፡፡

የጋራ ንቅናቄያችን ይህ በአማራ ተወላጆች ላይ የተከሰተውን ተግባር በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ላይ እንደተፈጸመ ወንጀል አድርጎ ነው የሚወስደው፡፡ እነዚህ ወገኖቻችን እንደ ኢትዮጵያዊነታቸው በየትኛውም የኢትዮጵያ ክልል የመኖር መብታቸው ሊጠበቅ ይገባል፡፡ በመሆኑም ከደቡብ ክልል በህወሃት/ኢህአዴግ ተጽዕኖ የተባረሩት ‹‹የአማራ ሰፋሪዎች›› ሳይሆኑ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ነን - ምክንያቱም ‹‹እነርሱ›› እና ‹‹እኛ›› የሚባል ነገር የለምና፤ ሁላችንም የኢትዮጵውያ ልጆች ነን፤ የአንዳችን አፍንጫ ሲመታ ሁላችንም እናለቅሳለንና፡፡ ‹‹ሁላችንም ነጻ ካልወጣን ማንም ብቻውን ነጻ ሊሆን አይችልምና!››

ልክ እነዚህ የአማራ ተወላጆች በደቡብ ሄደው ኑሯቸውን እንደመሠረቱ ሁሉ፤ በአሁኑ ጊዜም በሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች በጋምቤላና በቤንሻንጉል ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ እስካሁን ድረስ ግን የጋምቤላም ሆነ የቤንሻንጉል ነዋሪዎች የትግራይ ተወላጆችን ከክልላቸው አላባረሩም፤ በግዳጅ አላፈናቀሉም፡፡ እንዲያውም የመለስ አገዛዝ በእነዚህ ክልሎች የሚገኙ ቀደምት ነዋሪዎችን በመንደር ምስረታና ግዳጅ ሰፈራ በማፈናቀል መሬታቸውን ለቻይና፣ ሕንድና ሌሎች የውጪ አገር ዜጎች እየሰጠ ኢትዮጵያውያኑን ግን አገር፣ መሬትና መኖሪያ አልባ እያደረገ ነው፡፡

ነገር ግን ይህ አሁን በአማራ ተወላጆች ላይ የተፈጸመው ወንጀል በትግራይ ተወላጆች ላይ ቢፈጸመስ? ዛሬ የኦሮሚያ፣ የጋምቤላ፣ የቤንሻንጉልና የአፋር ኃላፊዎች በክልላቸው የሚገኙትን የትግራይ ተወላጆችን “የዓይናችሁ ቀለም አላማረንም” በማለት እንዲወጡ ትዕዛዝ ቢያስተላልፉ የአቶ መለስ ምላሽ ምን ይሆን? ለዚህ ነው የጋራ ንቅናቄያችን የአንዱ መጎዳት የሌላውም ነው የሚለው፡፡ በመሆኑም ይህ ዓይነት የግፍ እርምጃ በአማራ ተወላጆች ላይ ሲፈጸም በተለይ የትግራይ ተወላጆች ግምባር ቀደም በመሆን የተቃውሞ ድምጻቸውን ማሰማት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ‹‹በነጻ አውጪ›› ስም ኢትዮጵያን እየገዛ ከሚገኘው

**ህወሃት ጋር ከመተባበር ወይም እየተፈጸመ ለሚገኘው ወንጀል እንዳልሰማ ከመሆን ይልቅ ከመላው ኢትዮጵያዊና ከፍትህ ጋር በመቆም እንዲህ ዓይነቱን ወንጀል መቃወም፣ ማውገዝና መኮነን ይገባቸዋል፡፡ ‹‹ትግሬ ብሆንም ህወሃት እኔን አይወክልም፤ በስሜ ይህ እንዲሆን አልፈቅድም›› በማለት ‹‹የወያኔ ሓርነት›› ተግባር መፈጸም ወቅቱ የሚጠይቀው የጀግንነት ተግባር ነው - በተለይ ከትግራይ ተወላጆች፡፡ ሌሎችም እንዲሁ ከዘር ጠባብነት አርቆ በመመልከትና ‹‹ከነጻ አውጪ ግንባር›› ሣጥን በመውጣት እነዚህን ‹‹ምንም ይዛችሁ ስላልመጣችሁ ምንም ይዛችሁ አትሄዱም›› እየተባሉ ለዘመናት ያፈሩትን ንብረትና ሃብት እየተነጠቁ ለስቃይና ለእንግልት ከተዳረጉ ኢትዮጵውያን ጋር መቆም ይገባቸዋል፡፡ ‹‹የ. . . ነጻ አውጪ ግምባር›› እያሉ ለጠባብ ዓላማና ግብ ከመታገል ይልቅ ‹‹የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ነጻ አውጪ ግምባር›› ዓላማን በማንገብ ‹‹ከዘረኝነት ይልቅ ለሰብዓዊነት›› እንዲታገሉ የጋራ ንቅናቄያችን አጥብቆ ያሳስባል፡፡** ውሸትን ማጋለጥ፣ ወንጀልንና ወንጀለኞችን መጋፈጥ፣ ለፍትሕ መቆም የኢትዮጵያዊነታችን ግዴታ ብቻ ሳይሆን የሰብዓዊነታችን መለያ በመሆኑ በአንዱ ላይ የሚደርሰው ጥቃት በሁላችንም ላይ የደረሰ መሆኑን በመቀበል እንቃወመው፤ እናውግዘው፤ ከጫንቃችን ላይም እንዲወርድ እንታገለው፡፡

**የጋራ ንቅናቄያችን በአማራ ወገኖቻችን ላይ የተፈጸመውን በደልና ወንጀል እንዲሁም ፈጻሚዎቹን እየተከታተለ ለፍርድ የሚቀርቡበትን መረጃ መሰብሰቡን ይቀጥላል፡፡ በተጨማሪም ተጽዕኖ ማድረግ የሚችሉ የውጪ መንግሥታትና ድርጅቶችን ስለሁኔታው በማሳወቅና ድርጊቱን በማጋለጥ የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡** ከዚህ ባሻገር የጋራ ንቅናቄያችን የቆመበት መሠረቱ ሰብዓዊነትን የማስቀደም የትግል ጉዞ እንደመሆኑ ይህ ትግል ከምንጊዜውም በላይ በድል የሚጠናቀቅበት ዘመን መቃረብ እንዳለበት እናምናለን፡፡ **ሰብዓዊነት በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ይሰፍን ዘንድ ራሱ ሰብዓዊነት ጀግኖችን ይፈልጋል፤ አንጋሾችንም ይናፍቃል፡፡** ለዚህም ነው የጋራ ንቅናቄያችን ገና ከጅምሩ **‹‹ከጎሣ ይልቅ ለሰብዓዊነት ቅድሚያ እንስጥ››** በሚል መሪ መፈክር አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመመስረት የሚታገለው፡፡

በመከራና በስቃይ ላይ የሚገኙትን ወገኖቻችንን ፈጣሪ እንዲጠብቃቸውና ምህረቱን እንዲያወርድላቸው የሁላችንም ዕርዳታ አይለያቸው፡፡ ከሁሉ በላይ ግን ከፈጣሪ በተሰጠችንና በአያት ቅድመ አያቶቻችን ታፍራና ተከብራ የቆየችውን አገራችንን ሁሉም ዜጎች ያለምንም ፍርሃትና ጭንቀት ለመኖር የሚችሉባት ለማድረግ እንድንችል ይርዳን፡፡

## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

****************************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

